


# የስፖንሰርሽፕ ኣመልካቾችን ለቃለ መጠይቅ ማዘጋጀት

ከካናዳ የቪዛ ሃለፊዎች ጋር የሚደረግ ቃለ መጠይቅ የስደተኞች ስፖንሰርሽፕ ማመልከቻውን ለመወሰን ጠቃሚ ሂደት ነው። ኣመልካቾች ብደብዳቤ በኢመይል ወይም በተሌፎን ለቃለ መጠይቅ ይጋበዛሉ። የቃለ መጠይቁ ዓላማ ኣመልካቹ በግል የስደተኞች የስፖንሰርሽፕ ፕሮግራም ውስጥ ለመግባት ብቃት እንዳለውና ወደ ካናዳ ለመምጣት የሚፈቀድለት ስለመሆኑንና፣ እንዲሁም ካናዳ ለስደተኛው ሁኔታ የተሻለ ምርጫ መሆኑን ለማረጋገጥ ነው።

የቢዛ ኦፊሰሩ ውሳኔ በቃለ መጠይቁ ውጤት ላይ የሚሞረከስ በመሆኑ፣ ይህ ሰነድ[1] ለቃለ መጠይቅ እንዴት መዘጋጀት እንደሚያስፈልግ፣ በቃለ መጠይቁ ግዜና ከዚያም በኋላም መደረግ ስለሚገባቸው ኣንዳንድ ኣስፈላጊ የሆኑ ምክሮችን ይለግሳል። ይህ ሰነድ የህግ ምክር እንዳልሆነ ማስተዋል ያስፈልጋል፣ ሆኖም ከቪዛ ኦፊሰር ጋር ስለሚደረገው ቃለመጠይቅ ለመዘጋጀት እንደ ጠቃሚ መምሪያ ሊጠቅም ይችላል።

## ከቃለ መጠይቁ በፊት፥

የማመልከቻው **ቅጅዎችንና** ኬዝዎን ለማጠናከር ለቪዛ ጽ/ቤቱ ያስረከቡዋቸው **ሌሎች ኣጋዥ ሰነዶችንም** በጥንቃቄ ደግመው ይመልከቱ። ቅጅዎቹ ብእጅዎ ከሌሉ፣ ስፖንሰሮችዎን ብፍጥነት ኣሳውቀው ሰንዶቹን እንዲያገኙ ማድረግ ይችላሉ። ማመልከቻውንና ኣጋዥ ሰነዶችን በሚያጤኑበት ግዜ የሚከተሉትን ነገሮች ትኩረት ይስጡባቸው።

- ፎርሙ ላይ የተመለከተውን የቤተሰብ ይዘት እንደተመለከተው ነውን? የማመልከቻ ፎርሞች ላይ ያልተጠቀሱ ለውጦች ካሉ (ጋብቻ፣ የተወለደ ህጻን ወይም በሞት የተለየ ኣባል)፣ የቪዛ ጽ/ቤቱንና (የርስዎ ስፖንሰሮችን) ከቃለ መጠይቁ በፊት ማሰወቅ ያስፈልጋል።
- በማመልከቻው ላይ ሁሉ የቤተሰብ ኣባላት ማለት የት እንዳሉ የማይታወቁትንና ሞተው ይሆናሉም የተባሉትንም ጭምር መጠቀስ ኣለባቸው። በማመልከቻው ላይ (ከእርሶ ጋር የሚሄድ ቢሆንም ባይሆንም) ያልተጠቀሰ የቤተሰብ ኣባል መኖሩን ከተመለከቱ ለቪዛ ጽ/ቤቱና ለስፖንሰሮችዎ ብፍጥነት ያሳውቁ።
- በማመልከቻው ላይ ያሉ መረጃዎች ትክክለኛና ግዜያቸውን የጠበቁ መሆናቸውን ያረጋግጡ። በፎርሙ ላይ ስህተቶች ካገኙ ለቪዛ ጽ/ቤቱና ለስፖንሰሮችዎ ከቃለ መጠይቁ በፊት ያሳውቁ።
- ሁሉንም ያልዎት ለኪዝዎ ማጠንከሪያ ጠቃሚ የሆኑ ደጋፊ ሰነዶች መቅረባቸውን ያረጋግጡ።

## የኣጋዥ ሰነዶች ለምሳሌ የሚከተሉት ሊሆኑ ይችላሉ።

- የግል ታሪክዎን ማረጋገጫ (የዜና ኣንቀጾች፣ ደብዳቤዎች የማስፈራርያ ጽሑፍች ከቤተሰብና ጓደኞች የተላኩ ደብዳቤዎች፣ የፖሊስ ሪፖርት ወዘተ...

[1] ይህ ዶክመንት (ሰነድ) በማኒቶባ ኢንተርፈይዝ ካውንስል (MIIC)፣ የስደተኛታት ቤ/ጽ (Office of Refugees)፣ ኣርቿዲዮሲስ ኦፍ ቶሮንቶ (ORAT)፣ ካናድያን ካውንስል ፎር ረፉዩጅስ (CCR) ኣቐዲሞም የተዘጋጀ መምርያ መሰረት በማድረግ የተዘጋጀ ነው።

- ከርስዎ ጋር በተመሳሳይ ሁኔታ የነበሩ ምን እንደተደረገላቸው የሚያስረዱ ሰነዶች (ለምሳሌ እንደ ስደተኛ እውቅና የተሰጣቸው ዘመዶች)
- ብእጅዎ ያሉ የመታውቅያ ሰነዶች
- የጋብቻና የቤተሰብ ብዛትን የሚያሳዩ ሰነዶች (የጋብቻ ወይ ፍች ሰርተፊኬቶች፣ የልጆችዎ የልደትና የጥምቀት ሰነዶች
- ብዩኤንኤችዚኣር (UNHCR) ለርስዎ የተሰጡ ሰነዶችና ደብዳቤዎች ፣
- በሚኖሩበት ኣገር ያሉበትን ሁኔታ የሚያመለክቱ ሰነዶች
- ኣሁን ባሉበት ኣገር ለመኖር ያለብዎትን ችግር የሚያሳዩ ሰነዶች እና፣
- ኣስፈላጊ የጤና የስነ ኣእምሮ ችግር የሚያመለክት ሰነዶች (የሓኪም ሪፖርት፣ የሕክምና ውጤቶች ወዘተ)

## የስደተኛነት ታሪከውን ጠንቅቀው ይወቁ፣

የቪዛ ማጣት (መንሳት) ዋናኛ ምክንያት የተዛባ መረጃና ምስክርናት መስጠት ነው። ለምሳሌ በቃለ መጠይቁ ወቅት የሚሰጡ መረጃ በማመልከቻ ሰነዱ ላይ ከሰፈረው የተለየ ሲሆን ማለት ነው። ስለዚ በማምልከቻ ፎርሙ ለይ የሰፈረውን የግል ታሪከዎን በጥንቃቄ ያንብቡ። ታሪከዎን በሚያነቡበት ወቅት ለሚከተሉት ነጥቦች ትኩረት ይስጡ፤:

- እርሶዎንና ቤተሰቦን የሚመለከቱ ገጠመኞች ትክክል ስለመሆናቸውንና ቀናቶቹ በትክክል መስፈራቸውን ማረጋገጥ፣
- ታሪከዎን በሚገባ ያስታውሱ። በቃለ መጠይቁ ግዜ ሊረሱት የሚችሉትን ጠቃሚ የሆኑ በቤተሰቦችዎ ላይ የተፈረጹ ፍጻሜዎች፣ ግዜ፣ ቀን፣ ቦታ በዝርዝር ያስቀምጥዋቸው።
- **ከምታምኑት ሰው ጋር ቃለ መጠይቁን ይለማመዱት።** በትውልድ ኣገርዎ የነበርዎትን ህይወትንና ኣገር ለቆ ለመሄድ ያስገደድዎት ምክኒያትን በተመለከተ ሊጠይቅዎ ይችላል።
- **በግል ታሪከዎ ስህተት ካገኙ፣ ወይንም ኣስፈላጊ የሆኑ ገጠመኞች ወይም ፍጻሜዎች ካልተጠቀሱ፣ የቪዛ ጽ/ቤቱንና ስፖንሰሮችዎን ከቃለ መጠይቁ በፊት ያሳውቁ።**
- በርስዎ እና በቤተሰቦችዎ ላይ የተፈጸሙ ጠቃሚ ገጠመኞች በታሪከዎ ውስጥ ኣለመስፈራቸውን በተመለከተ **ተጨማሪ መረጃዎች** ካሉ ለ**ቪዛ ጽ/ቤቱንና ስፖንሰረችዎን በጽሑፍ በፍጥነት ያሳውቁ።**

## በቃለ መጠይቅ ግዜ፣

የካናዳ የቪዛ ጽ/ቤት የቃለ መጠይቁን ቀን፣ ሰኣት፣ ቦታ ያሳውቅዎታል። <u>የቃለ መጠይቁን ቀን እንዳያሳልፉት</u>።

- በተጠቀሰው ቀንና ሰኣት ይድረሱ። መዘግየት የለብዎትም፣ ቢያንስ ከግማሽ ሰኣት ኣስቀድመው ቦታው ላይ መድረስ ይኖርበዎታል።
- በካናዳዊ የቪዛ ኦፊሰር ነው ቃለ መጠይቅ የሚደረግላቸው። ኣስተርጓሚ እንዲኖር ጠይቀው ከሆነ እርሱም ኣብሮት ክፍሉ ውስጥ ከርስዎ ጋር ይኖራል።

- የቪዛ ኦፊሰሩ፣  ጥገኝነት የጠየቁበትን ምክኒያት በወቅቱ በትውልድ ኣገርዎ ስላለው ሁኔታና ስለ ጥገኝነት ጥያቄዎን ይጠይቆታል። ከትውልድ ኣገርዎ ለምን እንደወጡ፣ ለምን መመለስ እንደማይችሉና በወቅቱ ያሉበት ኣገር ለምን መኖር እንደማይችሉ ይጠይቆታል። በተጨማሪም ስለ ትምህርት ደረጃዎ፣ የስራ ልምድዎ፣ የቤተሰብ ህይወትዎ የእንግሊዘኛና ፈረንሳይኛ ቋንቋ ችሎታዎ፣ ስለ ካናዳና ያልዎት እውቀትና ካናዳ ለመስፈር የመረጡበትን ምክኒያት በተመለከት ሊጠይቅዎት ይችላል።

## በቃለ መጠይቁ ግዜ ምን ማድረግ ይኖርበዎታል?

- ቃለ መጠይቅ የሚያደርግልዎትን የኢምግሬሽን ኦፊሰር ኣይፍሩት፣ ሲናገሩ ኦፊሰሩ እየተመለከቱ ይሁን፣ ኣቀርቅረው ኣይናገሩ፣ የስሜታውነት ሁኔታ ካልገጠመዎት በስተቀር፣
- የቪዛ ኦፊሰሩ ለሚጠይቅዎት ጥያቄ እርሱ ላይ ሙሉ እምነት በመጣል የተማላና እውነቱን መልስ ይስጡት፣ በተጨማሪም መልስዎ ግልጽና ያልተንዛዛ መሆን ይኖርበታል።
- ጥያቄው ካልገባዎት ኦፊሰሩ እንዲደግምልዎትና በሌላ ኣገላለጽ እንዲያቀርብልዎት ይጠይቁት፣ ማፈር የለብዎትም።
- **ታሪክዎን ኣያጋንኑ፣ ቀለል ያል ቢመስልም ሃቁን ይናገሩ፣ የውሸት መረጃ መስጠት የኢምግሬሽን ማመልከቻዎትን ተቀባይነት እንዳይኖረው ሊያደርገው ይችላል።**
- ለርስዎ ተራ እውቀት ብለው የሚያስቡት ነገር የቪዛ ኦፊሰሩ ያውቀዋል ብለው ኣይገምቱ። ኦፊሰሩ ማወቅ ይኖርበታል ብለው የሚያስቡት ሁሉ ይንገሩት። በተለይም ኣንዳንድ ለታሪክዎ ጠቃሚ የሆኑ ለየት ያሉ የልምድ የባህላዊ ሁኔታዎች ለኦፊሰሩ ይንገሩት።
- ማመልከቻው ላይ የተጠቃለሉ የቤተሰብዎ ኣባላት ወደ ኣገር ቤት ከተመለሱ እነርሱም ላይ ሊያጋጥሙ ስለሚችሉ ኣደጋዎች ጭምር ኦፊሰሩን ይንገሩት፣ ይህ የልጅዎችዎን ኣደጋም ያጠቃልላል።
- ኣስቀድመው ያስረከቧቸ ሰነዶች ካነበሩ መኖራቸው ለታሪክዎ ኣጋዥች መሆናቸውን የቪዛ ኦፊሰሩን ያስታውሱት፣
- በቤተሰብዎ ይዘት ለውጦች ካሉ የቪዛ ኦፊሰሩን ያሳውቁት፣ በቅርብ ግዜ ካገቡ ወይም ልጅ ከተወደ፣ ኦፊሰሩን ያሳውቁት፣ ካላሳወቁት ኣዲሶቹ የቤተሰብ ኣባላት ሌላ ግዜ ወደ እርስዎ እንዲመጡ ላይፈቀድላቸው ይችላል።
- የመደናገጥና የመበሳጨት ሁኔታ ከገጠምዎ እና ለመረጋጋት ትንሽ እረፍት ካስፈለገዎ ማፈር ወይ መፍራት የለብዎትም መጠየቅ ይችላሉ።
- **ኦፊሰሩን ለመንገር ኣስፈላጊ የሚሉትን ሁሉ ሳይናገሩ ከቃለ መጠይቁ ቦት ኣይውጡ።** ወደ ኣገርዎ ቢመለሱ ሊገጥመዎ የሚችል ኣደጋ ሁሉ በቃለ መጠይቁ ወቅት ለቪዛ ኦፊሰሩ ሳይናገሩ ቢቀሩ ኦፊሰሩ ውሳኔ በሚወስድበት ግዜ ግምት ውስጥ ላያስገባቸው ይችላል።

## <u>ከኣስተርጓሚ ጋር ስለመስራት፣</u>

እንግሊዘኛ ወይ ፈረንሳይኛ የማይናገሩ ከሆነ በቃለ መጠይቁ ግዜ አስተርጓሚው ሊረዳዎ ይችላል። **በቃለ መጠይቁ ግዜ አስተርጓሚ የሚጠቀሙ ከሆነ፥**

- አስተርጓሚው የሚናገረውን እንደሚገባዎ እሱም እርሶም የሚናገሩትን እንድሚገባው አረጋግጡ፣
- ሁሉንም ጥያቄዎች በግልጽ ይመልሱ፣ አስተርጓሚው የምትናገሩትን ቃላት ሁሉ እንዲተረጉመው መልስዎን አጫጭር ያርጉት፣ አስተርጓሚው መልስዎትን እንዲያሳጥረው ወይንም ግድፈት እንዲያደርግ አይፈቀድለትም።
- የሃይማኖት፣ ባህል፣ ወይ ዘር ማንነትን ሳይመለከቱ **በአስተርጓሚው ፊት እውነትን መናገር አይፍሩ፣** አተርጓሚው የቪዛ ኦፊሰሩ ላይ ተጽዕኖ ሊኖረው አይችልም።
- አስተርጓሚው ከተሳሳተ ወይም አንዳንድ መረጃዎች ካስቀረ፣ ቪዛ ኦፊሰሩን ወድያውኑ ይንገሩት፣ ያስተርጓሚውን ስህተት ለማረም ለማቋረጥን አይፍሩ።
- አስተርጓሚው የትርጉም ስራውን በትክክል አይሰራም ብለው ካመኑ፣ እባክዎን የቪዛ ኦፊሰሩን ያስታውቁ። ለምሳሌ አስተርጓሚው እንደ እርስዎ አንድ ቋንቋ የማይናገር ከሆነና አለመግባባት ከተፈጠረ፣ ወድያውኑ ሌላ አስተርጓሚ እንዲቀብልዎ በትህትና ይጠይቁ። አስተርጓሚው በስህተት መተርጎሙን ካወቁ ቃለ መጠይቁ እስኪያበቃ ድረስ አይጠብቁ።
- **ኦፊሰሩ በስህተት ከጠቀስዎ ወይ በስህተት ከገባው ለማረም መፍራት ወይም ማፈር የለብዎትም።**
- እርስዎ ሴት ከሆኑና አስተርጓሚው ወንድ ከሆነ ወይም (በግልባጩ) ከሆነ እና የግል ገጠመኝዎት እነርሱ ፊት መናገሩን ከልተመቸዎት (ካልፈለጉ፣ ኦፊሰሩን ስለዚህ ጉዳይ ለመናገር ማፈር ወይ መፍራት የለብዎትም።

## <u>*ወደ ቃለ መጠይቁ ምን ይዘው መጡ?*</u>

እባክዎን በእጅዎ ላይ ያሉትን ሰነዶች ኦርጅናሉን ያምጡ፣ እነሱ ደግሞ፣

- የእርስዎ እና ሌሎች በማመልከቻው ላይ ያሉ የቤተሰብዎ አባላት የመታወቅያ ሰነዶች
- የግል ታሪክዎን የሚደግፉና እርስዎ ወደ አገርዎ ከተመለሱ መንገላታት እንደሚደርስብዎ የሚያመለክቱ ሰነዶች፣
- አስቀድመው ያላስረከቡት አዲስ ዶክመንት ወደ ቃለ መጠይቁ ይዘው ከመጡ፣ አስቀድመው ያልላኩበትን ምክኒያት ማብራራት ይኖርበታል፣
- ከሰነዶች በእንግሊዘኛ ወይ ፈረንሳይኛ ካልሆኑ የትርጉሙ ቅጅ ማምጣት ይኖርበዎታል፣
- ከሚፈለጉት ሰነዶች በእጅዎ ላይ ከሌሉ ለምን ከእርስዎ ጋር እንደሌሉ ምክንያቱን ለኦፊሰሩ ለማብራራት መዘጋጀት ይኖርበዎታል።

## ከቃለ መጠይቁ በኋላ

ብዙውን ግዜ የቪዛ ኦፊሰሩ ውድያውኑ ውሳኔ ላይ ይደርስና በቃለ መጠይቁ ማብቂያ ሊነግርዎት ይችላል። ማመልከቻዎ ተቀባይነት ካገኘ ወድያው በቃለ መጠይቁ ማብቂያ የሕክምና ፎርም ይሰጥዎታል፣ ሆኖም ግን በአንዳንድ ግዜ የቪዛ ኦፊሰሩ ለመወሰን ተጨማሪ ግዜ ሊያስፈልገው ይችላል።

**በቃለ መጠይቁ መጨረሻ ላይ የሕክምና ፎርም ካልሰጥዎት፣**

- ቃለ መጠይቁ ካለቀ በኋላ ወደ ህንጻው ከገቡበት ጀምሮ የቃለ መጠይቁን ይዘት ባጭሩ ቢጽፉት ይመረጣል፣ ማለት የተጠየቁት ጥያቄዎች እና የሰጥዋቸውን መልሶች በዝርዝር ይጻፉዋቸው።
- በቃለ መጠይቁ ግዜ የሆነ ችግር ከነበረ፣ ለምሳሌ ኣንዳንድ ጠቃሚ መረጃዎችን ከረሱ ለቪዛ ጽ/ቤቱና ለስፖንሰሮችዎን በጽሑፍ ያሳውቁ፣ .
- ከቃለ መጥይቁ በኋላ ኣዲስ ኣጋዥ የሚሆን ደኩመንት ካገኙ እባክዎን ለቪዛ ጽ/ቤቱና ለስፖንሰሮችዎ ይላኩት።

Refugee Sponsorship Training Program
Tel: 416.290.1700, 1.877.290.1710
Fax: 416.290.1710
E-mail: info@rstp.ca, Website: www.rstp.ca